መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ(መ.ኢ.ሶ.ን.)
**ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE )**
**P.O.Box 14 01 17 . D-53056 Bonn . E-Mail: meisone@t-online.de**
www.meison.info

# ለጋራ አላማ ለጋራ ትግል

በኦሮሞ ወጣቶች የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በመቃወም የተጀመረውና በደርዘን ለሚቆጠሩ ዜጎች ህይወት ማለፍ ምክንያት የሆነው እንቅስቃሴ አሁን ባለው አዲስ ሁኔታ በአጀንዳውም በተሳትፎውም እየሰፋ ሲሄድ እየታዘብን ነው፡፡ ለዚህ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በወያኔ /ኢህአዴግ ግፈኛ አገዛዝ በተሰጠው የጭፍጨፋ ምላሽ የተነሳ ንቅናቄው በአጠቃላይ ቁጣን በተላበሰ መልክ ለዴሞክራሲ ወደሚለው ጥያቄ እየተቀየረ ነው፡፡ እንደዚህ በመሆኑም በአንድ በኩል በዚያው በኦሮምያ ክልል ከተማሪዎቹ ባሻገር ገበሬዎች፣ ሰራተኞች፣ ሴቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ከትግሉ እየተቀላቀሉ ሲሄዱ በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከኦሮሞ ወጣቶች አንድነት ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ፍትህና ዴሞክራሲ ለሚለው ለዚህ የጋራ የሆነ አጀንዳ የመንቀሳቀስ አዝማሚያ እያሳዩ ነው፡፡

ይህ በጎ ሂደት ቀጥሎ ለዚህ ፍትህና ዴሞክራሲ ለተጠማ ህዝባችን በጎ ውጤት እንዲያመጣ ዛሬ የሃገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች መክረው አንደኛ ንቅናቄው ሰፍቶ መላውን ህብረተሰብ የሚያካትትበትንና በእርግጥም የማይበገር ህዝባዊ የትግል ማእበል የሚሆንበትን፤ ሁለተኛ ደግሞ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ምን እናድርግ በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ተወያይተው አስቸኳይ መልስና የጋራ የትግል ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርባቸዋል፡፡

አንደኛ ትግሉ ሁሉን አቀፍ፣ ሁሉን አንቀሳቃሽ ህዝባዊ የትግል ማእበል እንዲሆን ምን ይደረግ ? በትግል አጀንዳውም ሆነ በተሳታፊው እየሰፋ የሄደው ትግል በዚህ እንዲቀጥል ዛሬ በዚህ ግፈኛ አገዛዝ የመብት ብቻ ሳይሆን የህልውና ቀውስ ውስጥ የገቡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ሁሉም ብሶታቸውን እያነገቡ እንዲንቀሳቀሱ ማበረታታትና ጥሪ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት ስራ አጡ ወጣት ለስራ፣ ገበሬው ለህልውናው ወሳኝ ለሆነው ለመሬት ይዞታ ዋስትና፣ ነጋዴውና ኢንቬስተሩ ከሙስናና ከአድልዎ ለተላቀቀ አሰራር፣ ሰራተኛው ለመብትና የጥቅም ጥያቄዎቹ፣ ምእመናን መንግስት በሃይማኖቶች አስተዳደር ጣልቃ ገብነቱን እንዲያቆም ወዘተ እየጠየቁ ትግላቸውን ማቀጣጠል ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡

ሁለተኛ በዚህ መልክ ብሶታቸውን እያነገቡነና መፍትሄ እየጠየቁ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉም ተራ በተራና በየፊናቸው የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ሁሉም ተራ በተራ የሚመቱበት አደገኛ ሁኔታ እንደሚከሰት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ይልቅ የሚያዋጣው አካሄድ ላይ ላዩን ሲታዩ የተሰበጣጠሩ የሚመስሉት የህብረተሰቡ ጥያቄዎች ምንጫቸው የተዛባና ጸረ ዴሞክራሲያዊው የወያኔ ኢህአዴግ ፖለቲካ መሆኑን ተገንዝበው ብሶትህ ብሶቴ በሚል አርማ በአንድነት ለአንድ አላማ በመቆም ሂደቱ ወደ ተባበረና በአንድ አቅጣጫ ወደሚገፋ ህዝባዊ ትግል እንዲቀየር መሞከር የግድ ይሆናል፡፡

ሶስተኛ በዚህ መልክ የሚቀሰቀሰው ትግል ደግሞ ከእነዚህ የተሰበጣጠሩ የመብትና የጥቅም ጥያቄዎች አልፎ መሄድ የኖርበታል፡፡ ለነዚህ ሁሉ ህዝባዊ ጥያቄዎች ዘላቂ የሆነ መፍትሄ የሚገኘው በሃገራችን ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ሲሰፍኑ ብቻ ስለሆነ የዚህ ህዝባዊ ትግል የፖለቲካ ገጽታ ከእለት እለት እየጎላ ሄዶ የስርአት ለውጥ በሚለው አጀንዳ ዙሪያ እየጎለበተ መሄድ ይኖርበታል፡፡

የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ይህንን የተቀነባበረና የተባበረ ህዝባዊ ትግል ለመቀስቀስ ግልጽ የሆነ ስትራቴጂ ነድፈው መንቀሳቀሳቸው አስቸጋሪም ቢሆን ቁልፍ የጊዜው ተግባር የመሆኑን ያህል ከዚህ የትግል መቀስቀስ ባሻገር ሌላም ታሪካዊ ተልእኮ ይጠብቃቸዋል፡፡ ይኸውም የዚህን ሰፊ ህዝባዊ ንቅናቄ ዘላቂነትና ለድል መብቃት ለማረጋገጥ መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ይመለከታል፡፡ ይህም አንደኛ ኢህአዴግ ይህንን ህዝባዊ እንቅስቃሴ በከፋፍለህ ግዛ ፖለሲ ካስፈለገ ደግሞ በደም ባህር ለማክሸፍ ሊጠቀም የሚችላቸውን አካሄዶች ከወዲሁ አጢኖ ለነዚህ የሚመጥን አጸፋ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ሁለተኛ ለዚህ ትግል አመራር ሊሰጡ በሚችሉ ሃይሎች (በግንባር ቀደምነት የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች፣ የፖለቲካና የሲቪክ ማህበራት መሪዎች ወዘተ ላይ) አይቀሬው የአፈና እርምጃ ሲወሰድ ትግሉን እንዳያዝረከርከውና አመራር አልባ በማድረግ እንዳያከስመው ምን ስትራቴጂ እንከተል የሚለውን ጥያቄ ከወዲሁ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲውን ለማክሸፍ አሁን በኦሮሞ ወጣቶች እንቅስቃሴ ዙሪያ የተከሰተው አንድነት በጣም ተስፋ የሚጣልበት ቢሆንም ይህ የአንድነትና የትብብር መንፈስ ዘላቂ እንዲሆንና እንዲጎለብት አንደኛ የኢህአዴግ መንግስት ይህንን ለመሰበር በራሱ ካድሬዎችም ሆነ በአንዳንድ ኦሮሞ አክራሪዎች የሚወሰዱና ህዝብን ከህዝብ ለማቃቃር የሚደረጉ ሙከራዎችን ነቅቶ መጠበቅና

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ(መ.ኢ.ሶ.ን.)
**ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE )**
**P.O.Box 14 01 17 . D-53056 Bonn . E-Mail: meisone@t-online.de**
www.meison.info

እንዳመጣጣቸው እየተከታተሉ ማክሸፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ለማድረግ በኦሮምያ በአሁኑ ወቅት በአማራው ብሄረሰብ አባላት ላይ የሚፈጸሙትን ግፎች ሁሉም ወገን - በተለይም እንዲህ አይነት ግፎች የሚፈጸሙት በኦሮሞ ህዝብ ስም በመሆኑ - የኦሮሞ ዴሞክራቶች በይፋ አውግዘው መውጣታቸውና ከዚህም ጋር ተያይዞ በአማራው ስም የተደራጁ ዴሞክራቶች በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚፈጸሙትን ግፎች በይፋ መቃወማቸው የአክራሪዎቹን ቅስም ለመስበርም ሆነ ለምንመኘው የህዝቦች የትግግዝና የወንድማማችነት መንፈስ መስፈንና ለትግሉ መሳካት ይህ ነው የማይባል አወንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ዛሬ ትግሉ እየሰፋ በጎንደር. በጎጃምና በሌሎች የሃገራችን ክፍሎች እየተከሰተ በመሆኑ በነዚህም አካባቢዎች እየተፈጸሙ ያሉትን አስከፊ የግድያ፣ የእስራትና የወከባ ዘመቻዎች ሁሉም በአንድ ድምጽ ሊያወግዛቸው ይገባል፡፡

ሌላው የተባበረ የህዝብ ትግልን ለማክሸፍ የኢህአዴግ መሪዎች የሚጠቀሙበት እኩይ ዘዴ በዚህ ለፍትህና መላ ህብረተሰቡን ወደ ዴሞክራሲ ለማሸጋገር በሚደረግ ትግል ፖሊሱ፣ ሰራዊቱና የደህንነቱ አባላት ብቻ ሳይሆኑ የኢህአዴግ አባላትም ሳያመነቱ በነሱ ጎን እስከመጨረሻው እንዲቆሙ በይፋም ሆነ በስውር የሚነዙትን ፕሮፓጋንዳ ጠንቅቆ ማወቅና መዋጋት ያስፈልጋል፡፡ የቅስቀሳው ዋና አላማ ለዚህ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ያልሆነ አጀንዳ በመስጠት ትግሉ በእነሱም ህልውና ላይ የተቃጣ አድርገው በማቅረብ እነዚህ ወገኖች በአልሞት ባይ ተጋዳይነት መንፈስ ተንቀሳቅሰው ይህንን ትግል እንዲወጉ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን አካሄድ ለመዋጋትና ለማክሸፍ ከፈለግን በማያቋርጥ ቅስቀሳ ትግሉ ዴሞክራሲና ብሄራዊ እርቅ የሰፈነባት ኢትዮጵያ ለመመስረት ስልጣን ላይ ተንሰራፍተው በአገርና በህዝብ ኪሳራ የግል ጥቅማቸውን ከሚንከባከቡ ጥቂት ሙሰኞችና ጸረ ህዝቦች ጋር እንደሆነና በሰራዊቱም ሆነ በኢህአዴግ አባላት ላይ የተቃጣ እንዳልሆነ፣ እነዚህ ሃይሎች በነገይቱ ዴሞክራሲያዊት ሃገራችን ቦታ እንደሚኖራቸው እያበሰሩ ትግሉን እንዲደባለቁ መወትወት ያስፈልጋል፡፡

እንቅስቃሴውን ለማዝረክረክ በአመራሮች ወይም በግንባር ቀደምነት በትግሉ የሚሳተፉ ዜጎች ላይ የሚያነጣጥር የአፈና ውርጅብኝ በእርግጥም የኢህአዴግ መሪዎች እንደሚመኙት (ከዚህ በፊትም በደንብ እንደታየው) የእንቅስቃሴውን መክሰም ወይም ህዝብ ለህዝብ የሚጋጭበት ትርምስ መልክ መያዝ እንዳያስከትል ያለን አንድ አማራጭ፤ ተነስ ታገል ለምንለው ህዝብ የዚህን ትግል ዘላቂ አላማ ምንነት ብቻ ሳይሆን፤ ወደዚህ በሚወስደው መንገድ በየደረጃው የምንታገልበትን የትግል አጀንዳና አካሄድ ከወዲሁ በግልጽ ማስጨበጥና ይህ አጀንዳና አካሄድ ምንም አይነት አፈና ሊደመስሰው በማይችል ሁኔታ በሚልዮኖች አእምሮ እንዲሰርጽ ማድረግ ይሆናል፡፡

ለዚህ ታሪካዊና አገራዊ ተልእኮ ብቁ ለመሆን ከዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች የሚጠበቀው የጊዜው አንገብጋቢ ተግባር በትግል ላይ ላለው ህዝባችን የምናስጨብጠው ግልጽ የሆነ የትግል አጀንዳ ምንነት ላይ መምከርና ለህዝቡ ይፋ ማድረግ ይሆናል፡፡ አሁን እንደሚታየው ሁሉም በየፊናው ህዝባችንን ተነስ ታገል እያለ በሚያሰራጨው መግለጫ የትም የሚደረስ አይመስለንም፡፡ በታጋዩ ህዝባችን ፊት ታአማኒነት እንዲኖረን ከፈለግን አመራር ማለት ምሳሌነትም ስለሆነ በአንድነት ተነስቶ እንዲታገልና እንዲሰዋ ጥሪ በምናደርግለት ህዝብ ፊት እኛም በአንድነት ቆመን በአንድ አቅጣጫ ለመታገል የተነሳን መሆናችንን ማሳየት ይጠበቅብናል፡፡

## የኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበር ትግል ያሸንፋል!!

ታሕሳሥ 19. 2008 ዓ.ም. (29.12.2015)